# የስልጣን ሽግግሩ ሰላማዊነት የዴሞክራሲያዊ ስርዓቱ ጥንካሬ ነፀብራቅ ነው

**አዱኛ ቱሳ**

የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን አገሪቱን የመሩት መለስ ዜናዊ ህልፈትን ተከትሎ አገራችንን በተመለከተ ክፉና ፀለምተኝነት የተሞላባቸው አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ አስተያየቶች ይንፀባረቁ የነበረው በአገር ውስጥና በውጭ አገራት በሚገኙ ፅንፈኛ የፖለቲካ ቡድኖችና የገዢው ፓርቲ የፖለቲካና ኢኮኖሚ መንገድ ባልተመቻቸው አንዳንድ የኒዮ ሊበራሉ እሳቤ አቀንቃኝ ዓለም አቀፍ ተቋማት አማካኝነት ነው፡፡

እነዚህ ኃይላት የመለስ ህልፈትን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ዓላማቸውን ለማስፈፀም የማያቋርጥ ጥረት ሲያደርጉ ሰንብተዋል፡፡ የፅንፈኞቹ እንቅስቃሴ የተስተዋለው ከመለስ ህልፈት በኋላ ብቻ አልነበረም፡፡ መለስ ታመዋል የሚለው ወሬ ከተሰማበት ጊዜ አንስቶም ብዙ ደክመዋል፡፡

ስልጣን በመያዝ አገር መምራት እንሻለን የሚሉት ፅንፈኞቹ የፖለቲካ ቡድኖችም ሆኑ በኢትዮጵያ ኒዮ ሊበራል የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ስርዓትን ለመትከል የሚውተረተሩት አካላት የተቀናጀ በሚመስል መልኩ ባካሄዱት ዘመቻ በህዝቡ ውስጥ አመፅ እንዲነሳ ሰብከዋል፤ የሌለ ታሪክ በመፈብረክ በገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ውስጥ የስልጣን ሽኩቻ ተፈጥሯል የሚል ፕሮፓጋንዳ ነዝተዋል፡፡

ጎን ለጎንም የመለስ ህልፈትን ፍፁም በተሳሳተ መልኩ እየተረጎሙ ከኢህአዴግ ማብቃት ጋር በማያያዝ ስልጣን ለመጋራት ተደጋጋሚ ጥሪዎችንም አስተጋብተዋል፡፡

የእንደዚህ ዓይነቶቹ ተግባራት ዓላማ በመንግስትና ህዝብ መካከል ጥርጣሬ እንዲፈጠር ብሎም በመንግስት ላይ አግባብ ያልሆነ ተቃውሞ እንዲያነሳ እንደዚሁም በህዝቡ ውስጥ ተስፋ የመቁረጥ ስሜትን በማነሳሳት ስርዓት አልበኝነት እንዲነግስ ማድረግ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

በእነርሱ እምነት ህዝቡ በመንግስት ላይ ከተነሳና በአገሪቱ ስርዓት አልበኝነት ከነገሰ አጋጣሚው የስልጣን ለውጥ ለማድረግ ያመቻል፤ በዚህም የሚመኙትን ስልጣን ለመጨበጥ እንችላለን የሚል ነው፡፡

የመለስ ህልፈት ከተሰማበት ዕለት ጀምሮ በኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ በአገሪቱ ውስጥ የነበረው ድባብና ከላይ የተጠቀሱት ፅንፈኛ አካላት የፈጠሩት የህልም ዓለም በእጅጉ የተለያዩ ነበሩ፡፡ የፅንፈኞቹ ሩጫ የስልጣን ወንበር ላይ ለመቀመጥ አመፅና ሁከት መቀስቀስ ሲሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ በሞት የተነጠቀውን መሪ ፍፁም በሆነ የሐዘን መንፈስ በክብር መሸኘት ነበር፡፡

በነዚያ ሁለትና ሶስት ሳምንታት ውስጥ የአገራችን ህዝብ የእለት ተግባራቱንም ጭምር በአግባቡ እየከወነ መሪውን በማሰብ ነበር ያሳለፈው፡፡ ፅንፈኞቹ በበኩላቸው ያለየሌለ አቅማቸውን ሁሉ በማሟጠጥ የህዝብ አመፅና ሁከትን ለመቀስቀስ በዘርፈ ብዙ ጥረቶች ተጠምደው ነው ያሳለፉት፡፡

ያም ሆኖ ግን የመለስ ህልፈት በመላው የኢትዮጵያ ምድር ቁጭትና ሐዘንን ከመፍጠሩና መሪው የጀመሩትን የለውጥ ጎዳና አጠናክሮ ለመቀጠል ድምፁን ከፍ አድርጎ ቃል ኪዳን ከመግባት ውጭ የአገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ከተጠበቀውም በላይ አዎንታዊ ነበር፡፡  አገሪቱን የሚመራው መንግስትም ፀጥታንና መረጋጋትን ከማጠናከር አኳያ ከወትሮው በተለየ የወሰደው እርምጃም አልነበረም፡፡

ፅንፈኞቹ የገመቱት ታንክ በአዲስ አበባም ሆነ በሌሎች የአገሪቱ ጎዳናዎች አልታዩም፡፡ እንኳን ታንክ ይቅርና የጦር መሳሪያ ያነገተ የፀጥታ ኃይል በህዝቡ መሃል ተፈልጎ አይገኝም ነበር፡፡ እንዲያውም አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በህዝቡ ማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ የሚከሰቱ ጥቃቅን ወንጀሎች እንኳ የቀነሱበት ሁኔታ ነበር የተስተዋለው፡፡

ህዝቡ ፅንፈኛና ፍፁም አደገኛ ለሆነው ለእነዚህ አካላት የጥፋት ዘመቻ ጆሮውን አልሰጠም፡፡ ህዝቡ በሞት የተለየውን መሪ በታላቅ ክብር ተሰናበተ፡፡ የአገሪቱ መሪዎችም የስልጣን ሽግግሩን በከፍተኛ መረጋጋትና ሰላም አካሄዱ፡፡

የኢትዮጵያ ፓርላማ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ ባካሄደው ጉባኤው የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ተክተው እንዲሰሩ አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝን ሰይሟል፡፡ ይህ የስልጣን ሽግግር የተካሄደበት መንገድ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጭምር የተወደሰ ነው፡፡ የተለያዩ አገራት መሪዎችና ዲፕሎማቶች በሰጡት አስተያየት እንደገለፁት በኢትዮጵያ የተከናወነው የስልጣን ሽግግር ፍፁም ሰላማዊና ከፍተኛ መግባባት የተሞላበት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ስናይ ይህ የመጀመሪያችን ነው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ በአገራችን የስልጣን ርክክብም ታይቶ አያውቅም፡፡ አንዱ ሲያልፍ ሌላው ስልጣኑን ለመጨበጥ ሲባል ደም ማፍሰስ፣ ያለፈው የገነባውን በማፍረስ ከዜሮ መጀመር የተለመደ የአገራችን ታሪክ ነበር፡፡ አሁን ግን ይህ ታሪካችን ተለውጧል፡፡  ተቃዋሚዎቻችን ግን ይህ ጊዜ ያለፈበትና ፍፁም ኋላ ቀር የሆነ አስተሳሰብ አሁንም ድረስ እንደተጠናወታቸው ይገኛል፡፡

አሁን ያለው የፖለቲካ ስርዓት በዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የተገነባ ነው፡፡ ባለፉት 20 ዓመታት ከውጭና ከውስጥ ይጋረጡበት የነበረውን አያሌ ፈተና አልፎ ጥልቀትንና ጥንካሬን እያጎለበተ የመጣ ዴሞክራሲ በአገራችን መሰረቱ ተጥሏል፡፡

በተለይ ከመለስ ማለፍ ጋር በተያያዘ በአገራችን ሰሞኑን እየታየ ያለው የፖለቲካ ድባብ በመላው ኢትዮጵያ ህዝብ መንፈስ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ በተጨባጭ መታየት መጀመሩን ያመላክታል፡፡ ከዚህም ባሻገር የሰሞኑ ድባበ ህዝቡ በአገሪቱ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ስርዓት ላይ ያለው እምነትና አጋርነት ጠንካራ መሆኑን በእርግጠኝነት ለመናገርም ያስደፍራል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ለስርዓቱ ይሁንታን ብቻ ሳይሆን አለኝታነቱንም ጭምር ነው እያሳየ የሚገኘው፡፡ ይህ ህዝባዊ ተቀባይነትና የመተማመን ስሜት የመጣው ያለአንዳች ምክንያት አይደለም፡፡ የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ስርዓቱ ለኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ፍፁም ያመቸ፣ ህዝቡንም ተጠቃሚ ያደረገ በመሆኑ እንጂ፡፡

በዚህች አገር ሁለንተናዊ ጉዳዮች ከህዝብ የሚልቅ ዳኛና ፈራጅ የለም፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት በኢትዮጵያ የሚታየውና የአገሪቱ ባለቤት ከሆነው ህዝብም በማያወላዳ መልኩ የተንፀባረቀው እውነታ ይህ ነው፡፡ እንግዲህ ሀቁ ይህ ነው፡፡ ለዚህች አገር ይሁንታ መስጠት የሚችለው ህዝቡ ብቻ ነው፡፡ ህዝቡም ይሁንታውን በተግባር ጭምር በማረጋገጥ ላይ ይገኛል፡፡

ፅንፈኞቹ ተቃዋሚዎችም ሆኑ በሰብአዊ መብት ጥበቃ ስም የሚንቀሳቀሱ አንዳንድ ዓለም አቀፍ ተቋማት መቆርቆራቸው እውነት ለሰብአዊ መብት፣ የህዝብ ልእልና፣ ሁለንተናዊ ጥቅምና ፍላጎት ከሆነ ይህንን የህዝብ ስሜት ማክበር ይጠበቅባቸው ነበር፡፡

የመንግስትት አዎንታዊ እርምጃዎችና ውጤታማ ተግባራትን ከማጣጣል ተቆጥበው  በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ መቀበል አዋቂነት ነው፡፡

በሰብአዊ መብት ጥበቃ ስም የሚንቀሳቀሱት የውጭ ድርጅቶችም ሆኑ ከፊታቸው ከስልጣን በስተቀር ሌላ ነገር የማይታያቸው የሚመስሉት ፅንፈኞቹ የተቃዋሚ ፖለቲካ ቡድኖች ላለፉት ዓመታት ያለማቀቅረጥ ያካሄዱት የፈጠራ ስም ማጥፋት ዘመቻ በኢትዮጵያ ህዝቦች ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ በራሱ የአገሪቱ ህዝብ ስልጣን ላይ ላለው መንግስት ያላቸውን ይሁንታ በግልፅ ያሳያል፡፡

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ላለፉት 20 ዓመታት አገር በመምራት ሂደት ውስጥ ያለፉ ከመሆናቸውም በላይ ጥልቅ የሆነ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ናቸው፡፡ አቶ ኃይለማሪያም የክልል ርእሰ

መስተዳድር ከመሆን አልፈው የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የቅርብ አማካሪም ነበሩ፡፡ ላለፉት ሁለት ዓመታትም የአገሪቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በመሆን ኃላፊነታቸውን በትጋት የተወጡ መሆናቸውንም የሚታወቅ ነው፡፡

እንደመለስ ሁሉ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትራችንንም የወለዳቸው ኢህአዴግ ነው፡፡ የፖለቲካ አመራር ብቃታቸውም በዚሁ ድርጅት ውስጥ ተኮትኩቶ ነው የጎለበተው፡፡ በመሆኑም በቆየው የኢህአዴግ የአመራርና የአሰራር ባህል መሰረት አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር በመለስ አመራር ዘመን የተጀመሩትን የለውጥ መንገዶች አጠናክረው ይቀጥላሉ የሚል እምነት በብዙዎች ዘንድ አለ፡፡

መለስ በኢትዮጵያ ውስጥ ግዙፍ የሆነ ታሪክ ሰርተው አልፈዋል፡፡ ኢህአዴግም እርሳቸውን በመተካት ድርጅቱንና አገሪቱን የሚመራ አባሉን መርጧል፡፡ ምንም እንኳ ከመለስ ህልፈትና እርሳቸውን ከመተካት ጋር በተያያዘ በተለያዩ አካላት የተለያዩ ክፉ ሀሳቦችና ምኞቶች ቀርበው የነበረ ቢሆንም በተግባር ሁሉም መና ቀርተዋል፡፡

የአገራችን የፖለቲካ ስልጣን ሽግግር ፍፁም ሰላማዊ መሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ እየላቀ መምጣቱን የሚያመለክት መሆኑን ብዙዎች በመመስከር ላይ ናቸው፡፡ በማይጨበጥ የህልም ዓለም ውስጥ የሚባዝኑት ጽንፈኞቹም ሆኑ ለዓላማቸው ማስፈፀሚያ የሚጠቀሙባቸው የውጭ ኃይላት መሰረት የሌለው መላምትና የፈጠራ ታሪክ መክኖ የቀረውም በህዝቡ የዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ በመሸነፉ ነው፡፡

በየትኛውም ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ የፖለቲካ ስልጣን የሚያዘው በህዝብ ቀጥታ ምርጫ መሆኑ ለፅንፈኞቹ የአገራችን ፖለቲከኞችም ሆነ ለውጭ አጋሮቻቸው ይጠፉባቸዋል የሚል እምነት የለኝም፡፡

አገሪቱን የሚመራው መንግስት ስልጣን የያዘው በህገ መንግስቱ ላይ በተቀመጡት ዴሞክራሲያዊ መብቶች መሰረት በተካሄደ ምርጫ አማካኝነት ነው፡፡ መንግስቱን የሚመራው ድርጅት የህዝቡ ይሁንታ ተሰጥቶት ነው ስልጣኑን የያዘው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብም ይህንን በተግባሩ እያረጋገጠ ይገኛል፡፡ የአገራችንን የፖለቲካ ስልጣን የሚወስነው እያንዳንዱ ህዝብ ነው፡፡

ፅንፈኞቹ ግን ይህንን የህዝብ ፍላጎት በመናቅና ዴሞክራሲያዊውን የስልጣን ባለቤትነት ሽረው በማያቋርጥ የስልጣን መጋራት ተማፅኖ መጠመዳቸው ፍላጎታቸው ስልጣን፣ አስተሳሰባቸውም ኢ-ዴሞክራሲያዊ መሆኑን እንጂ የህዝብ ጥቅም አለመሆኑን ቁልፍ አድርጎ ያሳያል፡፡

የመለስ ህልፈትን ከኢህአዴግ ማብቃት ጋር በማያያዝ ስልጣን ለመጋራት የቀረቡት ተደጋጋሚ ጥሪዎች ትዝብት ላይ ጥሏቸዋል፡፡ ሰሞኑን የታየው እውነት ግን የአገሪቱ ህዝብም ሆነ ገዢው ፓርቲ ጭንቀትና ሐሳብ የስልጣን ወንበር መከፋፈል ሳይሆን ሀገር መለወጥ መሆኑን ነው፡፡

ሁኔታቸውን ለማጤን የሞከረ እነዚህ የፖለቲካ ቡድኖች የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ፣ ህዝቡንና ገዢውን ፓርቲ በወጉ አያውቁም፡፡ እንደእኔ አተያይ አላዋቂ የሚመስሉት ሆን ብለው ነው፡፡ የእለት ተለት ህልምና ቅዠታቸው የሆነውን የስልጣን ማማ ለመጨበጥ ገሃድ የሆነውን የኢትዮጵያ እውነት መገልበጥ፣ ካስፈለገም ህዝቡን ደም ማቃባት የሁል ጊዜ ተግባራቸው ነው፡፡ የሰሞኑንም ሆነ የከዚህ በፊቶቹ ተግባራቸውም ከዚሁ የሚመነጭ ነው፡፡ ይህ ህልማቸው ግን ከንቱ ሆኗል፡፡

ወደድንም ጠላን በዚህች አገር በመገንባት ላይ የሚገኘው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ጠንካራ መሰረት በመያዝ ላይ ነው፡፡ ህዝቡ ዘመናዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብን እያጎለበተ ኋላቀርና ፅንፈኛ አመለካከቶችን በገሃድ መፋለም ጀምሯል፡፡ በህዝብ ይሁንታ የመንግስት ስልጣንን የያዘው ድርጅትም ከመቼውም ጊዜ በላቀ ዴሞክራሲያዊነቱንና ውስጣዊ ብቃቱን በተግባር እያሳየ ይገኛል፡፡

በኢትዮጵያ መንግስት ሆኖ አገሪቱን የሚመራው ድርጅት እጅግ በበዙና በበረቱ ፈተናዎች ተፈትሾ ለዚህ የበቃ ነው፡፡ አገሪቱን የሚመራው ኢህአዴግ በጦር መሳሪያ ትጥቅና በወታደር ብዛት ግዝፈቱ ከሰሃራ በታች አፍሪካ አገራት ግንባር ቀደም የነበረውን የደርግ ኃይል ለመገርሰስ የቻለ መሆኑን ለሚያጤን ውስጣዊ ጥንካሬውንና የአመራር ብቃቱን መገንዘብ አያዳግተውም፡፡

ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ከመለስ ህልፈት ጋር በተያያዘ የተናፈሰበት ወሬ ባዶ ፈጠራ መሆኑን ሰሞኑን ያለአንዳች ኮሽታ ባካሄደው ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር በተግባር አሳይቷል፡፡ ይህንን የመሰለ የሰለጠነ ተግባር በመከወንም በአገሪቱ አዲስ ታሪክ አስመዝግቧል፡፡

የስልጣን ሽግግሩን በተመለከተ አሜሪካንን ጨምሮ የተለያዩ የዓለም አገራት መሪዎች ባስተላለፏቸው መልዕክቶች የኢትዮጵያ ህዝብንና የአገሪቱን የሚመራውን መንግስት አድንቀዋል፡፡ በኢትዮጵያ ጠንካራ መንግስትና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብን እያጎለበተ የመጣ ህዝብ መፈጠሩንም መስክረዋል፡፡

ፅንፈኞቹና አይዞህ ባዮቻቸው ለሚመኙት ስልጣን የመለስ ህልፈት ይከፍትልናል ያሉት ደጃፍ እንደተከረቸመባቸውና መላው ህዝብም ቅንጣት የምታህል ትኩረት እንደነፈጋቸው ሲገነዘቡ ክፉኛ ተደናግጠዋል፡፡ አፍንጫቸው ስር ቀርባ ታይታቸው የነበረችው ስልጣን የማትጨበጥ ህልም ሆና ታይታቸው የውርደት ማቃቸውን ተከናንበዋል፡፡

ሆኖም አሁንም ላለመሸነፍ በመውተርተር ላይ ናቸው፡፡ በስልጣን የቅዠት ዓለም ውስጥ ሆነው ሌላ መሰል ፈጠራ መንዛት ጀምረዋል፡፡ የአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትርን ሹመት በማጣጣልና በሌላ

ውዝግንብር ውስጥ ተጠምደዋል፡፡ ይህም እንደገና እነዚህ አካላት አገሪቱን፣ ህዝቦቿንና ገገርውን ፓርቲ በወጉ አያውቁትም እንድል አስገደደኝ፡፡

በብዙዎች እምነት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ እየተመዘገበ የሚገኘው አዲስ የታሪክ ምእራፍ ገገርው ፓርቲ ኢህአዴግ እጅግ ጠንካራ ድርጅት መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ አገሪቱ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ተቀባይነትንና እምነትን የተቸረ ጠንካራና ተፅእኖ ፈጣሪ መንግስት እንዲኖራት ያደረገውም የገገርው ፓርቲ ኢህአዴግ ውስጣዊ ጥንካሬ ነው፡፡

የዚህ አይነቱ ውጤታማና ተቀባይነት ያለው ጥንካሬ ምንጭ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና የፖለቲካ ብቃት እንጂ በምንም ተኣምር ፅንፈኞቹ እንደሚሉት አምባገነናዊነት ሊሆን አይችልም፡፡ የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ አላዋቂነትና በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ የሚዳክር ፅንፈኝነት ነው፡፡

የሰሞኑን የስልጣን ሽግግር በራሱ ለኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊነት፣ ውስጣዊ ጥንካሬና የአመራር ብቃት ማሳያ ሊሆን የሚችል በቂ ክስተት ነው፡፡

የተለያዩ አገራት መንግስታት ባወጡት መግለጫ በአገራችን ሰላማዊና ህገ መንግስታዊ የስልጣን ሽግግር መካሄዱን አድንቀዋል፡፡ ከአዲሱ የኢትዮጵያ መንግስት አመራር ጋርም በበለጠ ቅርበትና ትብብር ለመስራት ዝግጁ መሆናቸውንም አገራረቱ አስታውቀዋል፡፡

ከአገራችን ወቅታዊ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ከተለያዩ አካላት የሚቀርቡት አስተያየቶችም የፅንፈኞቹን የህልም አለም መላምት ውድቅ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

በፈረንሳይ ፓሪስ ውስጥ በሚገኝ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ የማኅበራዊ ሳይንስ ረዳት ፕሮፌሰርና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጥናት ማዕከል ዳይሬክተር የነበሩት ፕሮፌሰር ኤሉዋ ፊኬ ፤ “በመለስ ዜናዊ ድንገተኛ ሞት የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰጠው ምላሽ ብሔራዊ ሐዘን ምን ያህል ክብር እንዳለው፣ ሽግግሩን እንደምን በሰላማዊ ሁኔታ እየተካሄደ እንደሆነ ሚዛናዊነቱን ጠብቆ በአዎንታዊ መልኩ ታይቷል፤" ብለዋል።

ፕሮፌሰሩ በማያያዝም፤ "መለስ ዜናዊ ጠንካራ የነበሩ ቢሆንም ሀገሪቱን በግል አልነበረም የመሩት፤ የፓርቲ መሪ ስለነበሩ የፓርቲውን አጀንዳ ነው ሲያስፈፅሙ የኖሩት፤ ኃይለ ማርያምም ይህንኑ እንዲያደርጉ ይጠበቃሉ፤” በማለትም ለአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ እንግሊዝኛ ቋንቋ ዝግጅት ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ የእንግሊዝ አምባሳደር ግርግ ዶሪ ከመለስ ህልፈት ጋር በተያያዘ በአገሪቱ ችግር ይፈጠራል ለሚሉ ወገኖች ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ሰሞኑን ከአንድ የአገር ውስጥ ጋዜጣ

ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ በኢትዮጵያ ያለው መንግስት ጠንካራ መሆኑንና የዚህ ዓይነቱ ክስተት ለችግር ያልዳረገው መሆኑን መስክረዋል፡፡

አምባሳደሩ በዚሁ አስተያየታቸው ኢትዮጵያ አንድ ሰው ማለት አለመሆኗን ጠቅሰው በአገሪቱ ብቃት ያለው መንግስት አለ በማለት ተናግረዋል፡፡ በማያያዝም አገሪቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱን ጨምሮ ወደፊት ሊያስኳዱት የሚችሉ በርካታ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ባለቤትም ናት ብለዋል፡፡

አምባሳደሩ እንዳሉት፤ "….ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በጥልቅ በሳልነታቸው ልዩ መሪ ነበሩ፤ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካም ድምፅ የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ አለመኖር በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ጉዳት ይኖረዋል፤ ለምሳሌ በአየር ንብረት ለውጥ አጀንዳ ላይ የሰሩት ተጠቃሽ ነው… ሆኖም ግን ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በህይወት አለመኖራቸው ክፍተት ይፈጥራል የሚለው አይታየኝም፤ አቶ መለስ ሀገሪቱን ብቻቸውን አልነበረም የሚመሩት፤ መንግስት እና የስራ ባልደረቦቻቸው እንዲሁም ብልህ እና ብቃት ያላቸው ሃላፊዎች ሀገሪቱን መምራት እና ማስተዳደሩን ይቀጥላሉ፡፡"

ከመለስ ህልፈት ጋር በተያያዘ በአገሪቱ ምንም ዓይነት መልክ ያለው የሰላም እጦትና ያለመረጋጋት ሁኔታ አለመታየቱ፤ ይልቁንም ህዝቡና መንግስት የእለት ተለት ተግባራቸውን በተለመደው መንገድ ሲያከናውኑ መታየቱም በተለያዩ የውጭ አካላት አድናቆት ተችሮታል፡፡

ሰሞኑን የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት ያሳዩት ተግባር አገሪቱን በዓለም መድረኮች ዘውትር የሚያስታውስ ታሪክ ነው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ በኢትዮጵያ የታየው የፖለቲካ ክስተት ከሌሎች የአፍሪካ አገራት መሰል ክስተቶች ጋር ሲወዳደር በእኔ እምነት ልዩ ስፍራ ሊጎናፀፍ የሚገባው ይመስለኛል፡፡

በብዙ የአፍሪካ አገራት መሪዎች ሲሞቱ የተለመደው ትእይንት የፖለቲካ ቡድኖች መናቆርና ስር የሰደደ ስርዓት አልበኝነት ነው፡፡ በአገራችን ግን ፍፁም ፀጥታ የሰፈነበት የስልጣን ሽግግር ነው የተከናወነው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በኢትዮጵያ ለጽንፈኝነት የሚሰጥ እድል ተንጠፍጥፎ ማለቁን የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

በአገራችን የተካሄደው የስልጣን ሽግግርና ከዚሁ ጋር በተያያዘ ህዝቡ ያንፀባርቅ የነበረው ስሜት ከመለስ ህልፈት በኋላ አገሪቱን የሚመራው ፓርቲ በስልጣን ይሻኮታል፣ በዚህም አማካኝነት ይፈረካከሳል፣ አገሪቱም ለከፋ ችግር ትጋለጣለች የሚል የማይጨበጥ መላ ምት አልመውና ህዝቡንም ወደስርአት አልበኝነት ተግባር እንዲገባ በመጎትጎት ለከረሙት፤ ይህም እውን እንዲሆን በመጠባበቅ ላይ ለነበሩት የአገራችን ፅንፈኞችና የውጭ አጋሮቻቸው ትልቅ መልእክት ነው፡፡

በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የተስተጋባው መልዕክት ከእንግዲህ በኢትዮጵያ ለስራ እንጂ ለአሉባልታና ለጽንፈኝነት ቦታ የለም የሚል ነው፡፡ በአገሪቱና ህዝቦቿ መንፈስ ውስጥም ዴሞክራሲያዊና አገራዊ አስተሳሰብ በእጅጉ እየጎለበተ መምጣቱንም እነዚህ አካላት ሊጨብጡት የሚገባ መልዕክት ይመስለኛል፡፡

የተወራውና በአገራችን አንዳንድ የተቃዋሚ ቡድኖች የተፈለገው ቀውስ መና ሆኖ የቀረው መንግስት ወይም ሌሎች አካላት ለእነዚህ አካላት የጥፋት ፕሮፓጋንዳ አፀፋዊ ፕሮፓጋንዳ ወይም ማስተባበያ ስለሰጡ አይደለም፡፡

ለነገሩ መሰረት ለሌለው ለዚህ የጥፋት ዘመቻ መልስ ሊሰጡ ቀትሮ ሁኔታውን ማጤን ለሞከረ ልባቸውን እንኳ ሰጥተው የተከታተሉትም አይመስልም፡፡ መላው የአገሪቱ ህዝብም ሆነ መንግስት ተጠምዶ የከረመው በሞት ለተለዩት ታላቅ መሪ ያደረበትን ሀዘንና አክብሮት በመግለፅ እንጂ ይነዛ ለነበረው ባዶ መላምትና መሰረተ ቢስ ትንበያ ምላሽ በመስጠት አይደለም፡፡ እንዲያውም እጅግ በሚገርም ሁኔታ ንቀት በተሞላበት መልኩ አሉባልታውንና መላምቱን ያጣጣለው ነበር የሚመስለው፡፡

ያም ሆነ ይህ ሲነዛ የከረመው መላምትና ትንበያ ፍፁም የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ መሰረተ ቢስና ቦዶ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በአገሪቱ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ በራሱ ሲስተጋባ የነበረውን የጥፋት ፕሮፓጋንዳ መዋጋትና ውድቅ ማድረግ ችሏል፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ተቋማዊ እየሆነ መምጣቱንና ህብረተሰቡም በዴሞክራሲ የሚያምን ከመሆን በላይ እጅግ ሲበዛ አርቆ አሳቢነቱን በግልፅ ያሳያል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ አስተዋይ ህዝብ ነው፡፡ የሚጠቅመውንም ሆነ የሚጎዳውን ጠንቅቆ የሚገነዘብ ህዝብ፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ምን እየተከናወነና ምን ዓይነት ለውጥ እየመጣ እንደሆነና በእጅጉ ይረዳል፡፡ በአገሪቱ ጨለማው እየተገፈፈ መሆኑን እያየ ነው፡፡ ይህ ጨለማ ሙሉ በሙሉ ተገፎ አገሪቱ በለውጥ ብርሃን የምትሞላበት ጊዜ ቅርብ መሆኑም ያለምንም ብዠታ እየታየው መሆኑን በአደባባይ በመመስከር ላይ ነው፡፡

ይህ የተስፋ ብርሃን እንዴትና በማን ትግል ሊቃረብ እንደቻለም በደንብ ያውቃል፡፡ ለዚህም ነው የመለስ ህልፈት ክፉኛ ያንገበገበውና ከልብ የመነጨ ወገናዊነቱን በእንባው ጭምር ያረጋገጠው፡፡

የዚህች አገር ህዝብ ካለፉት 20 ዓመታት የፖለቲካ ሂደት ብዙ ተምሯል፡፡ የተወሰነው የአገሪቱ ህብረተሰብ ክፍል የመንግስትን የእለት ተእለት ተግባራት ከማጣጣል አልፈው በአገሪቱ ተስፋ መቁረጥና ሁከት እንዲስፋፋ በሚሰብኩት የተለያዩ የተቃዋሚ ፖለቲካ ቡድኖችና በሰብአዊ መብት

ጥበቃ ስም የፖለቲካ ዓላማን በሚያራምዱ ዓለም አቀፍ ተቋማት የፈጠራ ክስ ግራ የተጋባበት ሁኔታን አሳልፏል፡፡

በሂደት ግን እውነቱ እየተገለፀለት ማን ትክክለኛ እንደሆነ መገንዘብ ከጀመረ ቆይቷል፡፡ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ዘርፍ የተመዘገበው አመርቂ ለውጥ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይም በ1997 ዓም በአገሪቱ የተካሄደውን አገር አቀፍ ምርጫ ተከትሎ እላይ በተገለፁት አካላት የተፈጠረው አግባብ ያልሆነና ኢዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ይህንን ህዝብ ብዙ አስተምሮታል፡፡

ህዝቡ ለዓመታት ያለማቋረጥ የሚዘንብበት የጥፋት ፕሮፓጋንዳ በቅጥፈት የተሞላና ከአገርና ህዝብ ፍቅር የመነጨ ሳይሆን ከስልጣን ጥማት የመነጨ መሆኑን ሙሉ በሙሉ መረዳት የጀመረውም ከዚህ አጋጣሚ በኋላ ይመስለኛል፡፡

በወቅቱ ከተለያዩ የውጭ ኃይላት ጋር በመተባበር ተሞክሮ የከሸፈው በአመጽ ላይ የተመሰረተ የመንግስት ለውጥ በአገሪቱ በብዙ መስዋእትነት የተገኘውን የዴሞክራሲ  ሂደት ፍፁም ከሆነ አደጋ ውስጥ የሚጥለው ብቻ ሳይሆን ህዝቦችን ዳግም ለማያባራ ደም መፋሰስ ይዳርጋቸው እንደነበር ተገንዝቧል፡፡

ይህ የህዝቡ አስተዋይነትና አርቆ አሳቢነት በተለይ በተከታዩ ምርጫ ማለትም በምርጫ 2002 ላይ በማያዳግም ሁኔታ በግልፅ ነበር የተንፀባረቀው፡፡ በዚህ ወቅት በተካሄደው ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ህዝቡ ከ96 በመቶ በላይ የሚሆነውን ድምፁን የሰጠው በአሁኑ ወቅት አገሪቱን በመምራት ላይ ለሚገኘው ፓርቲ ነው፡፡

በዚህም አብዛኛዎቹ የአገሪቱ ተቃዋሚዎች ይህችን አገር ለመምራት የሚያስችል ብቃትም ሆነ ዝግጁነት እንደሌላቸው ህዝቡ በግልፅ አሳይቷል፡፡ የሚነዛው የማጣጣልና የጥፋት ዘመቻም መሰረት የሌለው ነው ሲልም አስገንዝቧቸዋል፡፡

ፅንፈኛ የፖለቲካ አመለካከትን የሚያራምዱት አንዳንድ የአገራችን  ተቃዋሚዎችም ሆኑ የኒዮ ሊበራል አስተሳሰብ አራማጅ ተባባሪዎቻቸው ይህ እውነት ተገልጦላቸው በዚህ ወቅት ከጥፋት ዘመቻቸው መታቀብ ካልቻሉ መቼም ሊታቀቡ የሚችሉ አይመስለኝም፡፡ ያም ሆኖ ይህ መንገድ ምንም አይጠቅማቸውም፡፡ የአገሪቱ የስልጣን ባለቤት የሆነው ህዝብ ፍርዱን ሰጥቷል፡፡

በአሁኑ ወቅት በአገራችን ያለው የፖለቲካ ሁኔታ የሚያስረዳው ጽንፈኝነትን የማይሸከም ትውልድ መፈጠሩን ነው፡፡ ትውልዱ ጽንፈኝነትን መዋጋት በመጀመሩም ፅንፈኛ ፖለቲካዊ አመለካከት ከምድሪቱ እየተገፈፈ መሆኑንም ያመለክታል፡፡ በኢትዮጵያ ጠንካራ የዴሞክራሲ መሰረት እየተጣለ መሆኑንም ሂደቱ ግልፅ አድርጎ ያሳያል፡፡